የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ- የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 25
ADDIS ABABA- 21st February, 2005

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፵/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በተወሰኑ የወጪ ንግድ ዘርፎች ለተወሰነ ጊዜ ብቸኛ ውክልና መስጫ አዋጅ ...ገጽ ፫ሺ፶፫

## CONTENTS

**Proclamation No. 440/2005**

The Granting of Exclusive Agency on Certain Export Trade Sectors for a limited period of time Proclamation ........ Page 3053

### አዋጅ ቁጥር ፬፻፵/፲፱፻፺፯

### በተወሰኑ የወጪ ንግድ ዘርፎች ለተወሰነ ጊዜ ብቸኛ ውክልና ለመስጠት የወጣ አዋጅ

በተወሰኑ የወጪ ንግድ ዘርፎች ብቸኛ ውክልና በመስጠት ወደ አዳዲስ የውጭ ገበያዎች በስፋት ለመግባት የሚያስችል ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በተወሰኑ የወጪ ንግድ ዘርፎች ለተወሰነ ጊዜ ብቸኛ ውክልና መስጫ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "ላኪ" ማለት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ መሠረት የላኪነት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፣

፪/ "የውጭ ኩባንያ" ማለት በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተመዘገበና በውጭ ሀገር የሚገኝ ኩባንያ ነው፣

**፫. ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ዓላማ፣

### PROCLAMATION NO. 440/2005.

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE GRANTING OF EXCLUSIVE AGENCY ON CERTAIN EXPORT TRADE SECTORS FOR A LIMITED PERIOD OF TIME

**WHEREAS,** the granting of exclusive agency on certain export trade sectors could promote the extensive entry into new markets;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

1. **Short Title**
   This Proclamation may be cited as "the Granting of Exclusive Agency on Certain Export Trade Sectors for a limited period of time Proclamation No. 440/2005."
2. **Definitions**
   In this Proclamation:

   1/ "exporter" Means any person who has been given export license in accordance with the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 67/1997;

   2/ "foreign company" means a company registered in accordance with foreign laws and situated in a foreign country.

3. **Objectives**

   The Objectives of this Proclamation are:

፩/ እስከ አሁን በውስን ገበያዎች ውስጥ በወጪ ንግድ የተገኘው ጥቅም የሚጠበቀውን ያህል ባለመሆኑ የወጪ ንግድ የመዳረሻ ገበያ አድማስን በማስፋፋት አምራቹና ሀገሪቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ እና

፪/ ላኪዎች ታዋቂ ከሆኑ የውጭ ኩባንያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ወደ አዳዲስ ገበያዎች በስፋት ለመግባት የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ በአንጻሩ የውጭ ኩባንያዎቹ የሚያወጧቸውን የገበያ ማስፋፊያ ወጪዎች ለመመለስ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ለመስጠት ነው::

## ፬. ብቸኛ ውክልና ስለመስጠት

በተወሰነ የወጪ የንግድ ዘርፍ እምቅ ገበያ ባለው የውጭ ሀገር አዲስ ገበያ ለመግባት በተወሰኑ ላኪዎች እና በተቀባዩ የውጭ ሀገር ኩባንያ የተደረገ ስምምነትን መሠረት በማድረግ ሌሎች ላኪዎች ወደ ተመሳሳይ ገበያ ከተጠቀሰው የውጭ ኩባንያ ውጭ መግባት እንደማይችሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደሁኔታው ለተወሰኑ ዓመታት ብቸኛ ውክልና የሚሰጥ መመሪያ ማውጣት ይችላል::

## ፭. ክልከላ

ማንኛውም ላኪ ብቸኛ ውክልና በተሰጠባቸው የወጪ ንግድ ዘርፎች ብቸኛ ውክልና በተሰጠው የውጭ ኩባንያ አማካይነት ካልሆነ በቀር መላክ አይችልም::

## ፮. ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም::

## ፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1/ as the gain from export trade in limited markets is so far below expectation, to make producers and the country direct beneficiaries by expending the scope of target export market; and

2/ to make conducive business situation for exporters in order to enable them to extensively enter into new markets by creating ties with renowned foreign companies and to give such companies sufficient time to recover their expenses of market development.

## 4. The Granting of Exclusive Agency

Following agreements made between certain exporters and an importing foreign company to enter a new potential market in a foreign country, the Ministry of Trade and Industry may issue directive to grant exclusive agency to the foreign company; as it may be appropriate for a limited number of years; in certain export sectors, to prevent other exporters from entering the same market otherwise than through such foreign company.

## 5. Prohibition

No exporter may export in export trade sectors on which an exclusive agency has been granted, otherwise than through the foreign company to which the exclusive agency is granted.

## 6. Inapplicable Laws

No law shall, in so far as it is inconsistent with this proclamation, have force or effect in respect of situations provided for by this Proclamation.

## 7. Effective Date

The Proclamation shall come into force as of 21st day of February, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 21st day of February,2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት